ጥር 21ቀን 2015ዓም

# የብአዴን/አዴፓ/ብልፅግና አመጣጥና ተግባሩ!

በቅድሚያ ይህንን ለመፃፍ ያነሳሳኝ (1)ፋኖ ብአዴንን አሳዳጅ መሆን ሲገባው፣ባለመንቃቱ ተሳዳጅ ሆኖ መገኘቱ፣ (2) ሠሞኑን ልዩ ኃይሉ ነቅቶ በብአዴን ላይ አቋም ባለመውሠዱ፣በብአዴን ተባባሪነት፣ኦሮሞ! ሸዋና ወሎን ለመሠልቀጥ ያደረሠው የዘር ጭፍጨፋና የቤተ ክርስቲያኗ ችግር ነው።

እንደሚታወቀው ኢሕዴን ከኢሕአፓ አፈንግጦ የወጣና ከትህነግ ጋር አብሮ የሠራ መሆኑን ማንም ያውቃል።ይህንን ሲያደርጉ እነርሱም ሆኑ ትህነግ የግራ ፖለቲካ አራማጆች በመሆናቸው አብዮታዊ ዲሞክራሲ የሚለውን ፈሊጥ ተቀብለው፣"አማራው ጨቋኝ ነው" የሚለውን ከልባቸው አምነውበት ነው።

ነገር ግን ከኢሕዴን ወደብአዴን እንዴትና ለምን እንደተቀዬረ፣ቁጥሩ የማይናቅ አማራ በማህበራዊ ሚዲያ ጭምር በተደጋጋሚ ከዕውነታው ጋር የማይገናኝ ነገር ሲናገር በማድመጤ፣በቅድሚያ ዕውነታው ይኸውና።

መዐሕድ በእነፕሮፌሰር አሥራት ወልደዬስ መሥራችነትና መሪነት እየተጠናከረ መሄድ ሲጀምር፣ትህነግ! በወቅቱ መዐሕድን ከመሪው ከፕሮፌሠር አሥራት ጭምር፣ ለማጥፋት የተጠቀመበት አደገኛ መንገድ፣እንደትግሬው "አማራ ጨቋኝ ነው" ብሎ የሚያምነውን፣ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ የተጠመቀውን፣በኢትዮጵያ ሥም ሲመፃደቅ የነበረውን፣በአባልነት ትግሬውንም ጋላውንም ወላይታውንም ወዘተ የሚያግበሰብሰውን አማራ ጠሉን ድርጅት "ኢሕዴንን" በአንድ ቀን ጀምበር የአማራ ሥም ሠጥቶ ወደ "ብአዴን" ቀዬረው።

ለአማራ የቆመ መሥሎም አማራውን ከፋፍሎ እንዲያዳክም፣ ሕዝቡ ሥር ነቀል ለውጥ እንዳያመጣ በማዘናጋትና በማጭበርበር፣ በመግደልና በማሥገደል ተልዕኮ እንዲሠማራ አደረገው።ይህ ተልዕኮም፣የትግሬ ኢሕአዴግ በኦሮሞ ብልፅግና ቢተካም ባሠበት እንጅ አልተሻለውም።

እሥከዛሬዋ ዕለት ድረስ በክልሉ ህገ መንግሥት ውስጥ "ብሔራዊ ጭቆና አለ" ብሎ አሥፍሮ፣አማራውን ጨቋኝ አድርጎ ሥሎ የሚጓዝ ፀረ አማራ ድርጅት ነው።ለዚህ ማረጋገጫው የእሥከዛሬው ተግባሩ ነው።

በተጨማሪም አንዳንድ መሪዎቹ የተናገሩትን መጥቀሱ፣ለአማራው እንዳልቆሙ ይበልጥ ግልፅ ያደርገዋል።
(1) ትዕቢተኛው ታምራት ላይኔ የብአዴን መሪና ጠቅላይ ሚኒስቴር የነበረው ኦጋዴን ሄዶ፣አማራዎቹ ለሚፈጸምባቸው በደል አቤቱታ ሲያቀርቡ፣"አማራን እዚህ ምን አመጣው?" ብሎ ከመናገርም አልፎ፣ለኢትዮጵያ ሱማሌዎቹ ደግሞ "ሽርጣም የሚልህ ነፍጠኛ እዚህ ምን አመጣው?" ማለቱ አይዘነጋም።

(2) ሂሩት ካሳው የተባለችው ጉድ ደግሞ በቃለ መጠይቅ "አማራ ሌሎችን ጨቁኗል"ሥትል ጠያቂው እንዴት ሲላት፣ "የቋንቋ ጭቆና ነበር"አለች።ድንቁርናዋ ነው እንጅ፣የዛሬው ጌታዋ ኦሮሞ እሥከ ደርግ መምጣት ድረስ ከአፍ ቋንቋ በሥተቀር፣የፅሁፍ ፊደል አልነበረውም።የአፍ ቋንቋውንም ማንም አልከለከለውም።

የኦሮሞ የፊደል ቋንቋ በላቲን ይሁን ወይስ በግዕዝ የሚለውን ለመምረጥ ግምባር ቀደም ተዋናኝ ከነበሩት ውስጥ አንዱ ኃይሌ ፊዳ እንደነበር ፈረንሳዊት ሚሥቱ በአደባባይ አሥጥታዋለች።ይህ ደግሞ በደርግ ዘመን ነው።ያልነበረ የፅሁፍ ቋንቋ ምኑ ይጨቆናል? ሥለዚህ ሂሩት ካሳው በድንቁርናሽ እፈሪ።

(3) በቀቀኗ ዳግማዊት ሞገስ ደግሞ "የመሬት ላራሹና የብሔር ጥያቄዎች ተመልሰዋል፣የቀረው የዲሞክራሲ ጥያቄ ነው" ብላን አረፈች።ይህ አባባሏ ከጌቶቿ ከእነአቢይ እንደወረደ የተወሰደ ነው። ይህንን አባባል ዛሬ እነአቢይን የሚዘውረው ሌንጮ ባቲ ውጭ አገር ሲኖር በ SBS ራዲዮ ከ8ዓመት በፊት ተጠይቆ ከተናገረው ጋር አንድ ነው።

(4) ሥልጣን ላይ ሆኖ አማራን ያሥጠቃው፣እንደሽንኮር አገዳ መጥጠው ሲጥሉት ፋኖ! ማለት የጀመረው፣ ገዱ አንዳርጋቸው በአምናው በትግሬ ወረራ ወቅት "ህገ መንግሥቱ ምንም ችግር የለበትም፣ አማራውም ተጠቃሚ ነው" በማለት ለአፉ እንኳን ሳይቀፈው በድፍረት የተናገረ በዘሩ ላይ የፈረደ ፍጡር ነው።ዛሬ ሲጨንቀው "ፋኖ፣ፋኖ"ማለቱ ላይቀር።

(5) (ሀ)አጎብዳጁ አገኘሁ ተሻገር የብአዴን መሪ በነበረበት ወቅት "የኦሮሞ ወንድሞቻችን እየደሙ አማራውን ጠብቀውልናል " ብሎን አረፈው።ይህ "ምን ተናግሬ በኦሮሞ ልሸም" የሚል ፍጡር! በወለጋና በአገሪቱ በኦሮሞ የሚገደለውን አማራ፣ ኦሮሞዎቹ እነሽመልስ "እየገደሉ" ከሚያሥተባብሉት ጋር አንድ ነው።

(ለ) የአገኘሁ አሥተዛዛቢው ነገር ደግሞ፣የአማራ ሕዝብ ብሶቱን ለማሰማት በአንድነት ሠልፍ እንደወጣ አገኘሁ የሚያመልክበትን መሪውን አቢይን ሕዝቡ ሥለወቀሰበት፣"ሠልፉን አንዳንድ ኃይሎች ሊጠልፉት ሞክረዋል፣" ብሎ በወጣው ሠልፈኛ መካከል ጥርጣሬና መከፋፈልን ለመፍጠር አሣፋሪ መግለጫ መሥጠቱ አይካድም፡

(ሐ) ሌላው የአገኘሁ ጉድ ደግሞ በመተከል የሚያልቀውን አማራ ከሞት ከመታደግ ይልቅ፣ይባስ ብሎ "በቡሀ ላይ ቆረቆር "እንዲሉ የችግሩ ተሸካሚ የሆነውን ዘር "አማራ"ብሎ በስሙ መጥራት ተጠይፎ፣ "ዜጎች በማንነታቸው"እያለ የመሸፋፈኛና የማደናገሪያ ቃል በቀደመው በጥምቀት በዓል ላይ ሲረጭ ተደምጧል።

(መ)አገኘሁ ቀደም ሲል በወልቃይትና ራያ ጉዳይ የተናገረውን፣ወደ አቢይ ፌደራል ሲገባ ክዶ "በትግሬውና በኦነጉ ህገ መንግስት መሠረት ይፈታል"ብሎን አረፈው።ራሱን የሸጠ ፍጡር ነው።

(ሠ)የወለጋ አማራዎች! አገኘሁ እንዲረዳቸው ቢሞክሩም፣የሠጣቸው መልስ "አንደርስላችሁም፣ከዚያው ተሥማምታችሁ የምትባሉትን አሜን ብላችሁ ኑሩ!" ነው።

(6) (ሀ) ይልቃል ከፍያለ(አይልቅም ዝቅ አለ) ደግሞ ዮሐንስ ቧያለው! "በአማራው ህገ መንግሥት ውስጥ "ብሔራዊ ጭቆና አለ" ከሚለው ጀምሮ አማራውን የሚጎዱትን ሥህተቶች ተነጋግረን እናርም" የሚል ሀሳብ በድርጅት አባልነቱ ሲያቀርብ፣ ይልቃል!ዮሐንስ ለተናገራቸው፣ቀጥ ያለ መልስ መሥጠት አለዚያ በያድራል ይዞ ከማሥተካከል ይልቅ፣የዮሐንስን ሥም በመጥራት ጭምር ለማሸማቀቅ የሄደበት ዕርቀት አሣፋሪና ለአቢይ ማጎብደዱን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

ይልቃል! ቀጥሎም "ከሌሎቹ ጋር ተሥማምተን መኖር አለብን፣ አንድነታችን ወዘተ "የሚል ውሀ የማይቋጥር አባባል መሠንዘሩ፣ከተበርካኪ እንጅ ከጤነኛ አይምሮ አይወጣም።

ትህነግና ኦነግ መሰሎቻቸውን ይዘው በአማራው ላይ ዘመቱበት እንጅ እርሱ አልዘመተባቸው።እንዲህ ዓይነቱ ንግግር አማራ ሳይንቀሳቀስና ሳይመክት በአቢይና በይልቃል "መሬት ላይ የሌለ" የአንድነት ቃል ተሸብቦ፣እንዲያልቅ የአማራ ጠላቶች የሚያሴሩት ነው።

(ለ)የይልቃል የገዘፈው አሳፋሪ ነገር ደግሞ የአቢይን ቅጥፈት እንደወረደ ተቀብሎ "በብዙ ሽህ የሚቆጠር ሠራዊት፣ ኦነግ ሸኔን እየተዋጋ ነው"ብሎ ከዕውነት ሲጣላ ለአማራው ታስቦ እንደሚደረግ ሊነግረን ዳዳው።

(ሐ)ይልቃል!አሁን በቅርቡ ደግሞ ባህር ዳርና ናዝሬት ከኦሮሞው ጋር ተሰብስቦ፣ኦነግና የኦሮሞ ልዩኃይል ከቄሮው ጭምር በአማራው ላይ እንደዘመቱበት እየታወቀ፣ጌቶቹን ለማሥደሰት "ወለጋ ውስጥ እናንተ መረጃው ሥለሌላችሁ ነው እንጅ፣ኦነግ ሸኔ አማራን ሲገድል፣የአማራ ታጣቂዎችም ኦሮሞን እየገደሉ ነው" ብሎ ዋሽቶት አረፈው።

(7) ግዛቸው ሙሉነህ የሚባለው ጉድ ደግሞ ፋኖን በጠላትነት ፈርጆ "ጠላትን ድባቅ እንደመታ"ነግሮናል።

(8) ብዙዎቻችሁ የምታውቁት የእነግርማ የሽጥላ፣ሠማ ጥሩነህ፣አበባው፣ወዘተ ጉድም ተዘርዝሮ አያልቅም።

"ብአዴንም አማራ ነው" ለምትሉ የዋሆች !አማራነት!ከደምና ከአጥንት በላይ፣ለአማራው መቆምን ይጠይቃል።

መደምደሚያ! "እያንዳንዱ አማራ፣ፋኖን፣ልዩ ኃይሉንና ሚሊሺያውን ጨምሮ፣ ቁልጭ ያለ አቋም አለው" ለማለት የሚያሥደፍረው፣ የብአዴንን መሠረታዊ አመጣጥና ተግባር ጠንቅቆ ተረድቶ ድጋፉን ሲነፍገው፣ጠላትና ወዳጁን ሲለይ፣መሣሪያ ከመታጠቁ በፊት ነቅቶ ልቡን ሲያሥታጥቅ እና አደረጃጀቱን አሳምሮ በአማራ ላይ የተጫነውን ፀረ አማራ ሥርዓት: ህገ መንግሥትና የዘር ፌዴራሊዝም ለማሥወገድ ሲነሳ ብቻ ነው።ከዚህ ውጭ የሚደረጉት የእሥከዛሬው ያዝ ለቀቅ ተግባራት፣ አለመንቃታችን ያመጣቸው ናቸው።

አያሌው ፈንቴ